# “ለጥጃ” ጠመንጃ?

ሒትለር ወሰይጣን
ከጉድህ በአወጣን
ወይ የዛሬ ጣጣ
ደግሞ ምን አመጣ?
        ይመኝ ጀመረ
        ትናንት የነበረ።
ከሂትለር ምኩራብ
ኢድያሚን ድባብ
አክራሪ ሁቱ አምላክ
ለጥፋት የሚላክ
ኮዞቮ አሞራወች
ሰው ተቀላቢወች






ዳግማዊ አምሳያወች
ሁሉም ሲቆጠሩ
በታሪክ ነበሩ።
        ዳግማዊ አባ ሰይጣን
        ዛሬ ደግሞ አስቆጣን
        ለዚህ ትጉህ “ጥጃ”
        ተመኝለት ሳንጃ
        ቃሉ አልቀፈፈውም
        ትናንት ቢለምደውም
        ህዝባችንም ቢራብ
        ህልም ቢሆን ምግብ
        ሕጻናት ሲረግፉ
        አዛውንት ሲገፉ
        ሆኖ ከመ-ጤፉ
        ግድ አለው እንዴ እርሱ
        ከሞላለት ከርሱ?
ዛሬ በእርሱ ሚዛን
ሞልተን አልተገኘን
እርሱ ካልመራ አገር
ለእርሱ ሆኖ ሽብር
“ህዝብ ተቆጣ” አለ
ሃሰት ተናገረ
ከፈለግህ ተንጣጣ
“የግለሰብ ቁጣ”

ምንም አያመጣ።
አገር እያደገች
ዳዴ እያዘገመች
ለሚመራን መሪ
ታሪክም ዘካሪ
በመልካም ስም ጠሪ።
መሪየን ብትጠላው
“ክፉ ጥጃ” ያልከው
አንተ ነህ ወራዳ
የተመኘህ እዳ
የሚያስተውልቱ
ሁሉን የሚያውቁቱ
ዶክተር አሸብርን
የኢትዮጵያ ህዝብን
አትሰማ ደንቆሮው
መስማት ያልፈለግኸው
አይንህ የማያየው
የተጨፋፈንከው
ምላስህ መርዘኛ
የሆንከው ጉደኛ
በተመኘህለት በመሪየ ፋንታ
ሞትህን ያቀርበው የላይኛው ጌታ።
እኛስ መሪያችንን
እንወደዋለን እናከብረዋለን
ለቀቅ አድርግልን።




ደሳለኝ በርሄ
desberhe@gmail.com